# ግብን ማወቅ ስህተትን አለመድገም

የትግል ተመክሮን ማግኘት ፀጋ ነው:: በቅደሚያ የተጋድሎ ውጤት በመሆኑ:: በአብዛኛውም ጊዜ ደግሞ ይህ ተመክሮ የሚገኘው ታጋዩ ሕዝብ ደም ገብሮበት በመሆኑ:: ለምሳሌ በ1964 ዓ.ም. ኢሕአፓ ሲመሰረት ምንም እንኳን ቀደም ሲል የተማሪዎች እንቅስቃሴ ተመክሮ የነበረ ቢሆንም የተደራጀ የፖለቲካ ፓርቲን በተመለከተ ምንም ዓይነት ተመክሮ ባለመኖሩ ኢሕአፓ ከ ቲዎሪ ወይም ከመፅሀፍ ግንዛቤ ባሻገር ሀ ብሎ በተግባር መማር ነበረበት:: ይህም ብዙ ውጣ ውረድንና ስህተት መፈፀምን አስከትሏል:: ከዚያ ጊዜ ወዲህ ግን የበርካታ ዓመታት ሰፊ ተመክሮ ተገኝቷልና ስህተትን መድገም ምንም ማጠየቂያ አያገኝም::

ባለፈው የወያኔ ምርጫ የታየውን ይቅርና መለስ ብለን ወደ 1997 ዓይናችንን ብንቃኝ ከ 200 ያላነሰ ዜጋ ተፈጅቶ ወያኔ--ያውም በባዕዳን ድጋፍ--በህገወጥ ስልጣን ቀጥሏል:: የሰላምና ምርጫ መንገድ በወያኔ የማይሰራና ውድቅ የተደረገ አማራጭ ሆኖ በገሀድ ታይቶ ነበር:: ይህ ተመክሮ ቢኖርም፣ የምርጫው ህግና ኮሚሽን ባይቀየሩም እንደገና ምርጫ ብለው የተኮለኮሉና አልፎም እናሸንፋለን ብለው የቃዡም መኖራቸውን መታዘብ ግድ ሆኖብናል:: ይህ እንደገና መደረግ የሌለበት ስህተት ነው:: በዚህም ዙር ነፍስ ተገብሯል፣ የተሰቃዩና የታሰሩም ጥቂቶች አልነበሩም:: ግን የተገኘው ውጤት ከተጠበቀው በላይ የወያኔን ፀረ ዴሞክራሲነት ያጋለጠና የመድብለ ፓርቲን ጭምብል የሰባበረ ነው:: የወያኔ አንድ ፓርቲ አምባገነንነት ግልፅ ብሎ ቁልጭ ብሎ ለዓለም ሁሉ ታይቷል-- አስመስሎ እያጭበረበረ እንዲቀጥል የፈለጉት ባዕዳን ሳይቀሩ አፍረውበታል:: የኢትዮጵያ ሕዝብ መብቱንና ሀገሩን መቀማቱንም ዕብሪተኛው ወያኔ ምን ትሆን ምን ትሆኑ በሚል አሳይቷል:: ከዚህ ወዲህ በሰላም በምርጫ የሚለው አማራጭ የሙት ሙት መሆኑና የውርደት ጎዳና መሆኑን ወያኔ ራሱ በማያወላዳ መንገድ እየነገረ ባለበት ለመጪው አምስት ዓመት ምርጫ እንዘጋጅ ብሎ ሰበካ መጀመር ከስህተትም ስህተት በህዝብ ጎጂነት ና ወያኔን ጠቃሚነት የሚፈረጅ አቅዋም ነው:: ካለፈው ሂደት መማር ሲቻል ያጠፋነው ለምርጫው በበቂ አለመዘጋጀታችን ነው ብሎ መደምደም ራስን መገምገም ሳይሆን ራስን ለቀጣይ ባርነት ማዘጋጀት አሊያም ለወያኔ በተለጣፊነትና ሎሌነት ለመቀጠል መወሰን ተብሎ የሚወሰድ ነው:: የፖለቲካ ተቺና አዋቂ ነን ማለት የጀመሩ አንዳንዶችም ለተቃዋሚ ድርጅቶች አዲስ ዕድል መጥቷል--ለመጪው ምርጫ አምርሮ መዘጋጀት-- በሚል የሚሰነዝሩት ሀሳብ በእጅ አዙር ደረጃ ቢያንስ የወያኔ ጥንስስና ውላጅ መሆኑ የሚያከራክር አይደለም::

ታሪኩን የረሳ ስህተቱን ይደግማል ተብሏል:: ሕዝብና ሀገርን የሚመለከት ስህተት ደግሞ ጉዳቱ መቸም ቀላል አይሆንም:: በሰው ህይወት መቀለድና ሀገርንም ለአደጋ ማጋለጥ፣ ህልውናዋንም ማጥቃት ይሆናል:: ወያኔ እንደ ቅኝ ገዢ ሀይል ኢትዮጵያን በጠላትነት ፈርጆ ሊያደቃት የተቻለውን ሁሉ በማድረግ ላይ ነው:: ስለዚህም ሀገር ማዳንና ሕዝብን ባለመብት ማድረግ ተቆራኝተው ያሉ ግዳጆቸ ናቸው:: የኢትዮጵያን ህልውና የሚፃረሩ ሁሉ ይህን ግዳጅ የሚፃረሩ ናቸው--ከወያኔ ተጣላን አሉ አላሉ:: የኢትዮጵያን ህልውናና አንድነት ማረጋገጥ ቀዳሚ ግዳጃችን ሲሆን ይህ

ም ሀገር አድን ትግል በመሰረቱ ሀገርን አድኖ ለሌላ ወያኔ ለማስረከብ ሳይሆን የሕዝብን ሉዓላዊ ነት ለማረጋገጥና ዴሞክራሲያዊ ስርዓትን ለማስፈን መሆኑ መዘንጋት የለበትም:: ይህን መሰረት ያላደረገ ትግል ሀገርንም አያድን፣ ሕዝብንም አይታደግ ብንል ትክክል ነው:: በአሁኑ ጊዜ፣ ያን ሁሉ ተመክሮ ከገበየን በኋላ፣ ወያኔ ከቀለደብንና ሀገራችንን ካዋረደ በኋላ፣ ምርጫ የተባለውን ቧልት በተመለከተ እንኳን ወንበር አላቀምስም ብሎ ከታበየ በኋላ፣ ብዙ መቶ ዜጋ ካለቀና ብዙ ሺዎች ዛሬም በየማጎሪያው መከራ እየተቀበሉ እያሉ፣ ስንቱ ዜጋ በምስጢር እስር ቤቶች በተለይ ም በአዲስ አበባ በጨለማ ቤት ስየል እየተቀበለ እያለ፣ የወያኔ ዘረኛነት ብሶበት ለእልቂት የሚዳ ርግን ሁኔታ እያረጋገጠ መጥቶ ባለበት ተመልሶ ትልቁ የፖለቲካ ግንዛቤያችንና የቀሰምነው ትምህርት ለመጪው ምርጫ ፈርጠም ብሎ መዘጋጀት ነው ማለት በሕዝብ ላይ መቀለድና የወያ ኔን አገዛዝ ቀጣይነት መንከባከብ ነው:: ሌላ ትርጉም የለውም:: ወያኔን አጃቢ አቅዋም ነው:: መደረግ ያለበትን ትግል ሊያደናቅፍ የተነሳ ነውናም በበኩላችን አምርረን የምንቃወመውና የምንታገለውም ይሆናል::

19 ዓመትና ከዚያም በፊት ቢሆን የደደቢቱ ወያኔ ፀረ ሕዝብ ፀረ ኢትዮጵያ መሆኑ መቸም አከ ራካሪ ሆኖ አያውቅም:: በመጀመሪያ ያወጣው መርህ ግብር ትግራይን ገንጥሎ ነፃ የትግራይ ሬፐ ብሊክ ማቋቋም የሚል ነው:: ትግሌ ፀረ አማራ ነው፣ ግቤ መገንጠል ነው፣ኤርትራ የኢትዮጵያ ቅኝ ግዛት ናት፣ ከኦጋዴን እስከ አዳማ ናዝሬት ያለውና ባሌ፣ አሩሲንና ሀረርጌን የጠቀለለው መሬት የሶማሌ ግዛት ነው ወዘተ ብሎ የማለ የተገዘተና ከባዕዳን ጋር የተስማማ ቡድን ኢትዮጵያ ን ሀገር ብሎ ሊያሰብ ከቶም የማይጠበቅ ነበር:: ፍፁም ስልጣን መያዝ ደግሞ እንደተለመደው ወያኔን ይበልጥ አቆሸሸው፣ ይበልጥ በአፀያፊ ደረጃ ዘረኛ አደረገው እንጂ ቅንጣትም ኢትዮጵያዊ ነትንና ይሉኝታን አላለበሰውም:: ወያኔ በ19 ዓመት ድርጊቱ ፀረ ኢትዮጵያነቱን አረጋግጧል-- ይህን የማያወቅ ኢትዮጵያዊ የለም:: በቅርጫው ተካፋይ የሆኑ አንዳንድ ሆድ አደሮች ከክልል አንድ ውጪ ቢመጡም በዋና ደረጃ የወያኔ አገዛዝ ለክልል አንድ ተወላጅ አዲስ ከበርቴዎች ጥቅም የቆመ መሆኑን መሸፈን አይቻልም:: ሰፊውን የትግራይ ሕዝብ የሚወክል አገዛዝ ነው ባይባልም የተመሰረተውና የሚያራምደው የትግራይ ጠባብ ብሄረተኛነትን ነበር፣ ነውም:: ከትን ሽ አስከ ትልቁ የመስሪያ ቤት ሀላፊዎች፣ ጦርና ፖሊስ አዛዦች የትግራይ ተወላጆች መሆናቸው ፣ ውልደትና ዘር ጠቅሰው ተጠቃሚ የሚሆኑት በቅድሚያ የትግራይ ተወላጅ መሆናቸው የሚካ ድ አይደለም:: ከወያኔ ቁንጮ ተጋጨን ብለው የተነሱትም የቀድሞ የወያኔ አባሎች ዛሬም በአን ፃራዊ እንክብካቤና መብታቸውም ተጠብቆ ያለ መሆኑን ከኢሕአፓ አባላት መታሰርና ለፍርድ ተብዬ እንኳን አንዴም አለመቅረብ፣ ብዙዎች ለሀገራቸው እንዳይበቁ ከመደረጋቸው ጋር ስናወዳ ድረው ያለው ሁኔታ ግልፅ ሆኗል:: ዘረኝነት ሰፍኗል፣ የዚህ ተጠቃሚ የሆኑትም የክልል አንድ ምሁሮችና ነጋዴዎችም ከወያኔ ጎን ተሰልፈው የስልጣኑም የንግዱም የእርሻውም ባለቤት መሆና ቸውን ማየቱ ይበቃል:: ነውናም በተቃዋሚ ጎራ አለን የሚሉ የቀድሞ ወያኔዎችና የክልል አንድ ተወላጆች ዛሬም ቢሆን የወያኔውን ቁንጮ ማስወገድ ቢፈልጉም አገዛዙንና ዘረኛ ስርዓቱን ግን ለማስቀጠል መፈለጋቸው የሚደበቅ አይደለም:: ለዚህም ነው ምርጫ የተባለው ውድቅ

ሂደት ለይስሙላ አንድ ወንበር ለግሶ ሲያደባያቸው ምቱ አልሰማ ብሏቸው ለመጪው ምርጫ እንዘጋጅ ብለው የሚቀልዱት። ዋናውን ፀረ ወያኔ ትግል አሁንም ለማደናቀፍ የሚጥሩት።

በአሁኑ ጊዜ ለሁሉም ኢትዮጵያዊ ግልፅ ሆኖ የተገኘው ሀቅ ወያኔን በምርጫ ሳይሆን ማስወገድ የሚቻለውና የሚገባው በሁለገብ ትግል ማለትም በሕዝባዊ አመፅና በትጥቅ ትግል ነው የሚለው ነው። ከዚህ ሌላ ውጤትን የሚያስገኝ አማራጭ ወይም መንገድ የለም/ሊኖርም አይችልም። የኢትዮጵያ ሕዝብ ግቡና አላማው ዘረኛውን የወያኔ ስርዓት ማረቅ ማረም ሳይሆን መደምሰስ ነው። የመለስ ዜናዊና ወንጀለኛ ጓዶቹን በንፁሃኑ ደም የቀላውን እጅ መጨበጥና ከመይ ከመይ መባባል ሳይሆን አስሮ ለሕዝብ ፍርድ ማቅረብ ነው። ሀቀኛ የኢትዮጵያ ልጆችና ታጋዮች ከመለ ስና ጭፍሮቹ ጋር አይተቃቀፉም። ከነበረከት ጋር ውስኪ አይጨልጡም። የሕዝብን ጠላቶች አያቆላምጡም፤ ጓደኛዬ ብለውም አይጠሩም። ይህ ነው አንድ መሰረታዊው ሀቀኛውን ከአስመሳ ዩ መለያው። ጠላትን ጠላት ብሎ አምርሮ ይጠላል፤ ይዋጋል ወይስ ጠላትን ወዳጅ ብሎ ሲያመ ቸው አቅፎ ይሳሳማል--ለዚህ የሚሰጠው መልስ ማን ማንና ምን እንደሆነ ያሳየናል። ተቃዋሚ ነን ግና ደግሞ ከጥቅማ ጥቅሙም እንካፈላለን--ከስጋው ጠመኛ ነኝ ከመረቁ አውጡልኝ ፖለቲካ --የሚያዋጣ አይደለም።ዛሬ ወያኔ ባመቻቸው የዝርፊያ መድረክ ከበሮ የሚደልቁና ንዋይ አፈሰ ስን፤ሪዞርት ከፈትን፤ ቪላ ገነባን፤ሰፊ እርሻ ጀመርን ወዘተ በሚል ወደዱም ጠሉም የዝርፊያውና የሀገር ቅርጫው ተካፋይ የሆኑት ሁሉ ነገ  የወዳጃቸው የፍርድ ቀን ሲመጣ የጅራፉ ቀዳሚ ሰለባ እንዳይሆኑ ሊያሰጋቸው ይገባል። ያለው ሁኔታ  ወያኔን የበላይ አድርጎ ቢያሳይም ከምድር በታ ች እየተንጓጓ በመምጣት ላይ ያለው ሕዝባዊ ቁጣ ግን የከፋ የመሬት መንቀጥቀጥን አስከትሎ የወያኔን ስርዓት መሰባበሩና ማንኮታኮቱ አይቀርም። ይህ ደግሞ የተነገ ወዲያ ጉዳይ ሳይሆን የነገ ን ጥቆማ መሆኑን ማወቅ ያሻል። በምቾትና አስረሽ ምቺው የተደፈነ ጆሮ በሕዝብ  አመፅ ጩኸት ይከፈታል--ጊዜው ካለፈ በኋላ ይሆንና ግን የእበላ ባዩ ዋይ ዋይታው ሰሚን ያጣል።

ሕዝብ በአርምሞ የከፋ ሁኔታን ሂደት ሲታዘብ ጭቆናውን በደስታ ወይም በዝምታ የተቀበለ የሚመስላቸውና ሕዝብን የሚንቁ አሉ። ወያኔ ሕዝብን ስለናቀ የሀገራችንን መሬት ለሱዳን አሳል ፎ ሰጠ። ለግብፅም ከጓዳችን ከባሕር ዳር መሬት ሰጠው ። ለም መሬታችንን ለባዕድ ሸጠ ።የወሎ ና ጎንደር ለም መሬትን የትግራይ ብሎ ጠቀለለ። የክልል አንድ ባለሀብቶችን በጅማ፤ማንኩሽ፤ ሁመራና አብደራፊ፤ አዋሽና ደቡብ ሁሉ መሬት ላይ አሰማራ። በሕዝብ ላይ ፍጅትን አካሄደ ፤ ሺዎችን ለእስር ዳረገ፤ ብዙዎችንም አሳደደ ። በገዢው መደብ ዙሪያ ግን የሕዝብ ሰቆቃና መከራ ሳይሆን የጥቂቶች ደስታና መንደላቀቅ ገኖ ይታያል። የወያኔ ዕብሪት ለከት እንደሌለወም አይተ ናል። ወያኔ አደብ ገዝቶ፤ ፈሪሀ ሕዝብን አንፀባርቆ ይታረማል የሚለው ምኞት ከተቀበረ ቢያንስ 19 ዓመት አልፏል ብንል አንሳሳትም። ታዲያ የወያኔ ኢትዮጵያዊነት የሚል የሌለ ነገርን ፍለጋ ከድካም ሌላ ምን ሊያተርፍ? የወያኔ አገዛዝ ከነ ቅጥረኞቹና ተለጣፊዎቹ በአንድ በኩል ሰፊው የኢትዮጵያ ሕዝብ በሌላ በኩል ሆነው የማይታረቅ ቅራኔ አለ።ይህ ቅራኔ የሚፈታው በአሸናፊና በተሸናፊነት ደረጃ እንጂ በዕርቅ አይደለም። ማለትም ሕዝብ ከግቡ የሚደርሰው የወያኔን አገዛዝ

ገርስሶ በመጣል ብቻ ነው:: ለዚህ ግብ ያልተነሱና ያልተደራጁ ሁሉ፤ የሕዝብን ትግል አቅጣጫ ሊያስቀይሩ የሚጥሩ ሁሉ፤ ሳያፍሩ ለመጪው ምርጫ ተዘጋጁ ብለው ሊሰብኩ የተነሱ ሁሉ የሕዝ ብን ድል አወቁም አላወቁም በተጨባጭ የሚፃረሩ ናቸውና ሰይጣንን በፀሎት ወያኔን በብረት እንደተባለው ሁሉ እነዚህንም ትግል ጎጂዎች በሕዝብ ፊት እያጋለጥን ውጉዝ ከመ አርዮስ ልናደ ርጋቸው ይገባል:: ትጥቅ አስፈቺዎች ናቸውና::

የኢትዮጵያ ሕዝብ ግብ ሀገሩን ማዳን፤ ነፃነቱንና መብቱን ማስከበር ነው:: ይህም ማለት የወያኔን አገዛዝ በአመፅና በብረት መደምሰስ ማለት ነው:: ሌላ ትርጉም የለውም:: ሕዝብ ለዚህ ግብ መሳ ካት መነሳትና መደራጀት አለበት:: ስለ ጭቆናውና ውርደቱ መናገርና መጮህ ብቻ ሳይሆን ጨቋኙን ለማደባየት መነሺያ ጊዜ አሁን ነው:: የኢሕአፓ አባላትም ለዚህ ግብ ሕዝብን ለማደራ ጀት እንቅስቃሴያቸውን ከመቸውም ጊዜ በበለጠ በማጠናከርና በማስፋፋት ላይ ናቸውና በዚሁ ወሳኝ ተልዕኮ ስምሪታቸው ይቀጥላል:: የሕዝብ ጎራ የምንለውም የወያኔ አገዛዝ በሁለገብ ትግል መወገድ አለበት የሚለውን ነው:: የወያኔ አገዛዝ የሕዝብ ጠላት አይደለም የሚሉት ከሕዝብ ጎራ ገብተው የጠራውን እንዳያደፈርሱም መከላከል አለብን:: ሀይላችንን እንዳያዳክሙ፤ እንዳይበታት ኑን:: ጠላትን ለመዋጋት ስንነሳ ተመሳስለው ከውስጥ ሊቦረቡሩን የተነሱትን ቸል ልንል አይገባም :: ስህተት እንዳይደገምና የሕዝብ ግብ እንዳይደናቀፍ የሕዝብ ጎራ ከአስመሳዮችና ከወያኔ ጋር መወዳጀትን መፍትሄ ከሚሉ ክፍሎች መፅዳት አለበት:: ግዳጃችን ሀገርን ማዳን ነውና ባንዳ ተለይ ጥሩምባ መነፋቱ ጠቃሚና አስፈላጊም ነው:: የሕዝብ ጎራ ከፀዳና በጋራ ጠላት በወያኔ አገዛዝ ላይ አምርሮ ከተነሳ ግቡ በአጭር ጊዜ ይሟላል:: ለመጪው ምርጫ እንዘጋጅ ባዮችም ተንሳፈውና ተጋልጠው ይቀራሉ እንጂ ወደዱም ጠሉም ለወያኔ መሳሪያ እየሆኑ ወያኔ በሀገራች ን ላይ እንዲቀልድ ጋሻ ጃግሬዎች አይሆኑብንም::

ጠላታችን የወያኔ አገዛዝና ስርዓት ነው!
ግባችን ይህን አገዛዝ በሁለገብ ትግል መደምሰስ ነው!
ግባችን የኢትዮጵያን አንድነት አረጋግጦ ዴሞክራሲን ማስፈን ነው!!